Diploma Programme
Programme du diplôme
Programa del Diploma

# Amharic A: literature – Higher level – Paper 2
# Amharique A : littérature – Niveau supérieur – Épreuve 2
# Amhárico A: literatura – Nivel superior – Prueba 2

Monday 11 May 2015 (morning)
Lundi 11 mai 2015 (matin)
Lunes 11 de mayo de 2015 (mañana)

2 hours / 2 heures / 2 horas

---

### Instructions to candidates

- Do not open this examination paper until instructed to do so.
- Answer one essay question only. You must base your answer on at least two of the Part 3 works you have studied and compare and contrast these works in response to the question. Answers which are not based on a discussion of at least two Part 3 works will not score high marks.
- You are not permitted to bring copies of the works you have studied into the examination room.
- The maximum mark for this examination paper is **[25 marks]**.

### Instructions destinées aux candidats

- N’ouvrez pas cette épreuve avant d’y être autorisé(e).
- Traitez un seul sujet de composition. En basant votre réponse sur au moins deux des œuvres de la troisième partie que vous avez étudiées, vous devez comparer et opposer ces œuvres dans le cadre du sujet. Les réponses qui ne sont pas basées sur au moins deux des œuvres de la troisième partie n’obtiendront pas une note élevée.
- Vous n’êtes pas autorisé(e) à apporter des exemplaires des œuvres que vous avez étudiées dans la salle d’examen.
- Le nombre maximum de points pour cette épreuve d’examen est de **[25 points]**.

### Instrucciones para los alumnos

- No abra esta prueba hasta que se lo autoricen.
- Conteste una sola pregunta de redacción. Base su respuesta en al menos dos de las obras estudiadas de la Parte 3, comparándolas y contrastándolas en relación con la pregunta. Las respuestas que no se basen en al menos dos obras de la Parte 3 no recibirán una puntuación alta.
- No está permitido traer copias de las obras estudiadas a la sala de examen.
- La puntuación máxima para esta prueba de examen es **[25 puntos]**.



2215 – 0010

© International Baccalaureate Organization 2015

International Baccalaureate®
Baccalauréat International
Bachillerato Internacional

ከሚከተሉት **አንዱን** ጥያቄ መልስ(ሽ)። መልሱ በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) **ቢያንስ ሁለት** ስራዎች ላይ መመስረት አለበት። ስራዎቹን **በማወዳደርና በማነጻፀር** ጥያቄውን መልስ(ሽ)። በክፍል 3 ባጠናሀቸው (ባጠናሻቸው) ቢያንስ ሁለት ስራዎች ላይ **ያልተመሰረተ** መልስ ከፍተኛ ነጥብ **አያስገኝም**።

## ድራማ/ተውኔት

1. ድራማ ስሜትን መግለጫ ነው። ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በማነጻፀር ፀሀፊ ተውኔቶቹ ስሜትን እንዴት እንዳቀረቡና ለስራዎቻቸው ስኬታማነት እንዴት እንደተጠቀሙበት አስረዳ።

2. ከተውኔት የሚገኘውን ደስታ የሚወስኑት በቅደም ተከተል የሚቀርቡት ድርጊቶች ናቸው። ባጠናሃቸው ቢያንስ ሁለት ተውኔቶች ውስጥ ድርጊቶች እንዴት በቅደም ተከተል እንደቀረቡ ግለጽ።

3. እያንዳንዱ የተውኔት ገፀባህሪ የራሱ የሆነ ሰብእናና ልዩ የሆኑ መመሪያዎችና እምነቶች አሉት። ባጠናሃቸው ቢያንስ ሁለት ስራዎች ውስጥ ፀሀፊ ተውኔቶቹ እንዴትና ለምን አላማ እነዚህን በገፀባህርያት መካከል ያሉ ግልጽ ልዩነቶች እንደፈጠሩ አስረዳ።

## ረጅም ልቦለድ

4. ማናቸውም የልቦለድ ገፀባህርያት በህይወት የምናውቃቸውን ሰዎች መምሰል አለባቸው። ያነበብካቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በማነፃፀር ደራስያኑ ገፀባህርያቱን ሰዎችን እንዲመስሉ ያደረጉበትን መንገድና በዚህም ለልቦለዶቹ ያስገኙትን ጥቅም አብራራ።

5. ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ስራዎች በማነፃፀር ደራስያኑ ግልጽና የገሀዱን አለም የሚያሳዩ መቼቶች የሚያቀርቡበትን መንገድ አሳይ።

6. ልቦለድ የታሪኩን ቅደም ተከተል ጠብቆ ወደፊት ይራመዳል ወይም ወደፊትና ወደሁዋላ በመመላለስ የወቅቱንና ያለፈውን ታሪክ ያቀርባል። ይህንን አረፍተ ነገር መነሻ በማድረግ ባጠናሃቸው ቢያንስ ሁለት ስራዎች ውስጥ የታሪኮቹ ቅደም ተከተል ምን እንደሚመስል በማነፃፀር አስረዳ።

## ስነ ግጥም

7. ስራቸውን ባነበብክላቸው ቢያንስ ሁለት ገጣምያን ስራዎች ገጣማዎቹ እንደምን በተለያዩ መንገዶች ቀጥተኛ ያለመሆንን የግጥም አንድ ባህሪ እንዳቀረቡና ምን ያህልም እንደተሳካላቸው አሳይ::

8. ግጥሞች ጥልቅ ትርጉም የሚኖራቸው በገጣምያኑ ቋንቋ በተለይም ተለዋጭ ዘይቤ በመጠቀማቸው ነው:: ይህንን አረፍተ ነገር መሰረት በማድረግ ተለዋጭ ዘይቤና ሌሎችም ዘይበዎች ለግጥሞች እንደምን ጥልቅና የተለያየ ትርጉም ሊሰጡ እንደሚችሉ አሳይ:: ያጠናሃቸውን ቢያንስ ሁለት ገጣምያን ስራዎች ምሳሌ በማድረግ መልስህን ስጥ::

9. ገጣምያን ያለፈን ዘመን የማቅረብ ፍላጎታቸው ከፍተኛ ነው:: ስራቸውን ባጠናሀቸው ቢያንስ ሁለት ገጣምያን ስራዎች ውስጥ ያለፈ ዘመን እንዴትና ለምን አላማ እንደቀረበ አስረዳ::

## አጭር ልቦለድ

10. ስራዎቻቸውን ያጠናህላቸውን ቢያንስ ሁለት ደራስያን ስራዎች በማነጻጸር በአጭር ልቦለዶቹ ጡዘት እንዴት እንደቀረበና ምን ጥቅም እንዳስገኘ አስረዳ::

11. በአጭር ልቦለድ ተቃራኒ ገፀባህርያት መኖራቸው ታሪኩ ወደፊት እንዲራመድ ያደርጋል:: ባጠናሃቸው ቢያንስ ሁለት ደራስያን ስራዎች ውስጥ ተቃራኒ ገፀባህርያት የቀረቡበትን መንገድና በነሱ ምክንያት ታሪኩ  እንደምን ወደፊት እንደተራመደ አሳይ::

12. ስራዎቻቸውን ያጠናህላቸው ቢያንስ ሁለት ደራስያን ነጠላ ድርጊትን በመጠቀም የአጭር ልቦለዶቻቸውን ታሪክ ለመንገርና የስራዎቻቸውንም ዋና አላማ ለማሳካት እንዴት እንደቻሉ በንጻጻር አስረዳ::